# ስለአቶ አሰፋ ተስፋዬ ከማውቀው በጥቂቱ

ከወንድሙ መኰንን፣ ሎንደን፣ ታኅሣስ 22 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ሞት እንኳን ጨክኖ፣ ወስዶ ከሚያስቀር፤**
**ምናለ ደጋጉን፣ ዳግመኛ ቢፈጥር።**
**(ከጥላሁን ገሠሠ ዘፍኖች የተወሰደ)**

አቶ አሰፋ ተስፋዬን የማውቀው በግሪጎሪያውያን አቆጣጠር ከ1997 (፲፱፻፺፯ ዓ. ም.) ጀምሮ የስደት ኑሮአችንን በተያያዝንባት በሎንደን ከተማ ነበር። ከእስኮትላንድ ወደ ሎንዶን ስዛወር ላገሩ ባዳ፣ ለሕብረተሰቡ እንግዳ ስለነበርኩ፣ አቶ አሰፋ ተስፋየ በግሉ ሳያውቀኝ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሁኖ ተቀበሎኝ ኑሮዬን ካደላደሉልኝ ወንደምና እሆቶቼ አንዱ ነበር። ወዲያው የኢትዮጵያ ወቅታዊ  ወቅታዊ ሁነታ ያሳሰባቸው ሎንደን ኗሪ የሆኑ ኢዮጵያውያን በሲቪክ ማህበራት ዙሪያ በመሰባሰብ በሰሜን ሎንደን እና በደቡብ ሎንደን በተመሳሳይ ዓላማ ላይ ተመስረቶ የሚንቀሳቀስ ለአገር ተቆርቋሪ ስብሰብ አቋቋሙ። እያንዳንዱ ስብስብ በወይወሩ ሲገናኝ፣ በየሶስት ወር አንድ ጊዜ ግን አንድ ላይ ይሰበሰቡ ነበር። አቶ አሰፋ የደቡቡ ክንፍ አባል ሲሁን እኔ ደግም የሰሜኑ ክንፍ አባል  ነበርኩ። በኋላ ላይ ቁጥራችን እንዳሰብነው ሊያድግልን ባለመቻሉ፣ የደቡቡም የሰሜኑም አንድ ላይ ተቀላቅለን፣ እስከ ዛሬ ድረስ ለአገርና ለወገን አብረን እንደ ወንድም፣እንደ እህት እና እንደአንድ ቤተሰብ እየተሳስብን ብዙ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚና ተጨባጭ እንቅስቃሴዎችን አካሂደናል። በዚህ ለአገር ጉዳይ እንቅስቃሴ ስብስቡ ከተነሳበት ዓላማ አንዲት ጋት እንኳ ን ዝንፍ ሳይል አቶ አሰፋ ተስፋዬ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውቷል። ለአገሩና፣ ለወገኑ እንዲሁ እንደተብሰከሰከ፣ "እህህ!" እንዳለ፣ ከራሱ መሪር የሰደት እና የጤና እክለት ይልቅ ለኢትዮጵያ እንደ ሮጠ ኑሮ አይበሉት የስደት ኑሮን ኖራት።



አቶ አሰፋ ተስፋዬን የሕይወት ታሪክ ስንመረምር፣ አሳዳጊ አባቱ ግራዝማች ተስፋዬ ኃይለኛው  ሲሆኑ ወላጅ እናቱ ወይዘሮ ድንቂ አረርጉ ይባላሉ። በያኔው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ወስጥ በምትገኝ ጨፌ ዶንሳ በምትባለ ቦታ ነበር መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፵፮ (12 September 1953) አቶ አሰፋ የተወለደው።  እስከ 11ኛ ክፍል በአካባቢው ተምሮ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኘው ልዑል በዕደማርያም የዝግጅት ት/ቤት (Preparatory) በግሪጎሪያን አቆጣጠር ሰኔ 1972 ዓ. ም፣ 12ኛን ክፍልን ሲያጠናቅቅ ቀጥሎም በዚያው በይኒቨርሲቲ ሥር ከሚገኘው የአዲስ አበባ መምሕራን ኮሌጅ በ1974 ዓ. ም. በእግሊዝኛ አስተማሪነት በዲፕሎማ ተመርቋል። ከአምስት ዓመት በኋላም ወደ ዩኒቨርሲትይ ተመልሶ በኢንግሊዝኛ ትምሕርት ለሶስት ዓመታት ተከታትሎ በቢ. ኤ (BA in English Language)ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1982 ዓ. ም. ተመርቋል። የደህረ ምረቃ ተምሕርቱንም ኤድንብራ (ዩናትድ ኪግደም) ከሚገኘው ከዝነኛው ሞሬ ሀውስ ኮለጅ (**Moray House College, Edinburgh)** በድኅረ መረቃ ከፍተኛ ዲፕሎማ በ1992 ዓ. ም አጠናቋል።

ይኸ ወንድማችን፣ ከአዲስ አበባ መምሕራን ኮሌጅ ሲመረቅ አገልግሎት የጀመረው ሸዋ ውስጥ በሚገኘው አታየ ከፍተኛ ሁልተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በእንግሊዝኛ መምሕርነት ነበር። ከአምስት ዓመት የሥራ አገልግሎት በኋላ ወድ ዩኒቨርሲቲ ተመልሶ ሲመረቅ ከ1992 አ.ም ጅምሮ በተልያዩ ተምህርት ቤቶች በንግሊዝኛ መምሕርነት አገልግሏል። እነሱም ከ1982-1983 ድረስ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ (International Community School, Addis Ababa)፤ በ1983 ለአንድ ተርም አዲስ አበባ በሚገኘው በዝነኛው ቅዱስ ዮሰፍ ትምሕርት ቤት (St. Joseph School, Addis Ababa)፣ ከ1983 እስከ 1986፣ አርሲ በሚገኘው ጢቾ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት (Ticho High School, Arisi) በንግሊዝኛ ትምሕርት ርዕሰ መምሕርነት አገልግሏል። ከ1987 ዓ. ም. ጀምሮ ወደ ባሌ ክፍለ ሀገር ተዘዋውሮ፣ በሮቤ መምሕራን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት (Robe Teachers Training Institute, Bale) መጀምሪያ በቋንቋዎች ጥናት ደፓርትመንት ርእሰ መምሕርነት (**Language Department Head)**፤ ለአራት ዓመት ካገለገለ በኋላ ቀጥሎም ለሁለት ዓመታት በዚያ በሮቤ መምሕራን ማሰልጠኛ በዲነነት እስከ 1991 ዓ. ም አገልግሏል። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ይኸ ትልቅ ሰው፣ አንዲት ቀን እንኳን ተሳስቶ እንዲህ ነበርኩ ብሎ ሲያወረ ሰምተነውም አናውቅም ነበር። በአጠቃላይ፣ አሰፋ ተስፋዬ የሥራ ሰው ነበር ብል ማጋነን አይሆኑም።



አቶ አሰፋ፣ ለከፍተኛ ትምሕርት ወደ ኤድንብራ ሂዶ የድኅረ ምረቃ ትምህርቱን በ1992 ሲያጠናቅቅ በጊዜው አገር ውስጥ ይካሄድ የነበረው የፖሊቲካ ሁኔታ አገሪቱን ጭርሶ ወደአልተፈለገው አቅጥጫ በመምራቱ ተበሳጭቶ እንደ ወጣ እንዲቀር ግድ ብሎት እንደማንኛውም ስደተኛ ለንደን ቀረ (ሎንደን ኗሪ በሆኑት የኢትዮጵያ የአራዳ ስደተኞች አነጋገር፡ "ቀዘቀዘ")። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ በአንድ በኩል በበጎ ፈቃደኝነት የኢትዮጵያ ስደተኞችን ጉዳይ እየተከታተለ፣ በአማካሪነት፣ በአስተርጓሚነት ያለምንም ክፍያ አገልግሏል። በሌላ በኩል ግን በአገራችን ውስጥ ለሚደረገው የዲሞክራሲ ማስፈን ትግል ከማናንውም ኢትዮጵያዊ ባላነሰ ሁኔታ ተንቀሳቅሷል። ይኸ ትሁት ሰው የታመመን ሁሉ ሲጠይቅ፣ ሲያስታምም፣ ለተረበሹትንና የአዘኑትን ሲያጽናና ከራሱ ይልቅ ለአገሩ ልጆች ደኅነነት ሲጨነቅ፣ ሲሯሯጥ ጊዜውን አሳልፏል። አንድ ኢትዮጵያዊ ሲሞት አስከሬኑ ወደ አገር ቤት እንዲላክ በጊዜውም ሆነ በገንዘቡ ሲረዳ ያየን ወገኖቹ የኮራንበት ወንድማችን አድርጎታል። ችግር ሲፈጠር መጀመሪያ ደራሽ አሰፋ ተስፋዬ ነበር።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አስፋ ከሰብዓዊ እንክብካቤው ባሻገር ቀሳውስት፣ ዲያቆናት አና ምዕምናን የመሰከሩለት ንጽሕ የሀይማኖት ሰው ነበር። እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ከርዕስ አድባራት ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተለይቶ አያውቅም። የሀገሩና የወገኑ ፍቅር፣ የሀይማኖቱ ጽናት ወደር የማይገኝለት ደግ ሰው ነበር። በተለይ የኢትዮጵያ ጤና አገልግሎት ድርጅት ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት ያገለግል የነበረውን አስተዋጽዎውን የሚያስታውስት ጓደኞች ስልዚህ ወንድም ብዙ  የሚናገሩት አላቸው። አቶ ከፋለ ዓለሙ፣ የኢትዮጵያ የጤና ድጋፍ ማኅበር ስለ አቶ አሰፋ ተስፋየ የሚከተለውን ብለዋል።



“አቶ አሰፋ ተስፋዬ ለረጂም ጊዜ ለንደን ውስጥ በሚገኘው የኢትዮጵያ የጤና ድጋፍ ማህበር ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት በመሰማራት ለሚወዱት የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ዘርር ብዙና እግጅ ጠቃሚ ሥራዎችን አበርከተውል። ከሠሩአቸው ሥራዎች ውስጥ ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን እንጥቅስላን።

- በአዕምሮና በአካል ጤንነት ችግር ያለባቸውን በቤታቸውና በሆንስፒታል በመገኘት ጠይቀዋል/ረድተዋል
- የጤንነት ችግር ካለባቸው ጋር በቀጠሮ ቀናችው አብረው በመገኘት አስተርጉመዋል
- ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ከኢንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በመተርጎም ከፍርተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል
- በቢሮ ውስጥ እንግዶችን በተገቢ መንገደ በመቀበል ከማስተናገድቸውም በላይ በተላያዩ የቢሮ ሥራዎችን አከናውነዋል።

አቶ አሰፋ ትስፋየ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባሕል፣ ልምድና ስንልቦና ጠንቅቀው የምያውቁ ስልነበሩ፣ በሥራቸው ላይ በእድሜ ባልጠጎች፣ ግልማሶችና ወጣቶች ጭምረ በጣም የተወደዱና የተከበሩ ነበሩ።” በማለት ያስታውሱአቸዋል።

ወንድማችን የጤንነት ሁኔታ እየከፋ ቢሄድም አንድም ቀን አሞኛል ብሎ ሲማረር ሰምተንም አናቅም። የስኳር በሽታ እንዳለበት



ነግሮን ለምግቡ ቢቻ ሲጠነቀቅ እናያው ነበር እንጂ ሌላ ለክፉ ይሰጠዋል ብለን የገመትነው አንዳችም ነገር አልነበርም። ብቻ እንዴት እንደሆን ስንጠይቀው “ድኅና ነኝ፣ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ” ከማለት በስተቀር ሲማረር አላየነውም። አሰፋን ከምንም በላይ የሚጨንቀው ለዚያችው መከረኛ አገር ብቻ ነበር። ከ2007 ዓ. ም ወዲህ የሲቪክ ማኅበራት ስብስብ በተለየ መንገድ ስለተደራጀን የማኅበራችን ገንዘብ ያዥ ሆኖ ሲያገለግለን ነበር። ለማንኛውም መዋጮ እሱ የመጀመሪያው ነው። የኢትዮጵያ መመሕራን ማኅበር፣ የጋዜጠኞች መመሕራን ማኅበር፣ የኢትዮጵያው ሰብዓዊ መብት ጉባዔ እና ለሌችም ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ አስፋ ተስፋዬ የተጫወተው ሚና ቀላል አልነበረም። ወራዊ መዋጫችንን ስናዘገይበት እየተቆጣን ይቀበለን ነበር። ቀጥ አድርጎ ሂሳባችንን ተከታትሎ አንዷት ሳንቲም ስታቀር መዝግቦ ይዞልን እዚህ አድርሶናል። እሱን አይቶ የማይጽናና ስደተኛ አልነበረም። እዚህ ላይ አንድ ማንሳት የምፈልገው ነገር ቢኖር በ2001 ወያኔ እነ ፕሮፌሰር መስፍንን ዩኒቨርሲቲ ተናግራችሁ ወጣቱን ቀስቅሳችሁአል ተብለው በግፍ ሲታሠሩ፣ የረሀብ አድማ ስንመታ አብሮን ተርቦ የሰባዓዊ መብትን ጥሰት ለጋዜጠኞች፣ ለእንግሊዝ ሕብረተሰብና እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ያጋለጠ ሰው ነበር። ሌሊት የዝናብ ዶፍ ሲወርድብን፣ የስኳር በሽተኛው (Diabetics) የተገላቢጦች እኛን ያጽናናን ነበር።

በትግላችን ግንባር ቀደም ተሰላፊው ታግሎ አታጋይ ወንድማችን ያለወትሮው ሁለቴ ከስብሰባችን ቀረብን። በመጀመሪያ “ትንሽ አሞት” ሊመጣ እንዳልቻለ አስታውቆ ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ሲቀር፣ ከመህላችን አንድ ጓደኛችን እቤቱ ድረስ ሂዶ ጎበኘው። በግድ በፖሊስ ቤቱን አስከፍቶ የገባበት ሁኔታ ነበር። የግል ሀኪሞቹ በሽታውን ሳያገኙት ቀርተው አደገኛ ሁኔታ ላይ እንደነበር ተረዳን። አምቡላንስ ተጠርቶ ለአስቸውኳይ እርዳታ ወደ ሀኪም ቤት ሲወሰድ፣ ረቀቅ ያለ ምርመራ ተደርጎለት ሲያበቃ አስደንጋጭ ዜና አስደንጋጭ ዜና ደረሰን። ወንድማችን የግል ሐኪሞቹ ሳይረዱልት ቀርተው ለሁለት ወራት  በሽታው ሳይታወቅ ቀርቶ የወንደማችን ሕይወት አደገኛ ሁኔታ ላይ መድረሰን ተረዳን። ሕይወቱን ለማትረፍ እንደሚጥሩ አስረዱን። እኛም የወንደማችንን መታመም ሰምተን ተደናግጥን በያለንበት ስንጸልይ በፕሮግራማችን መሠረት አገራችን ውስጥ ስላለው የዲሞክራሲ እጦት ለአካባቢ ጉዳይ ኮንፈረንስ(Copenhagen Environmental Conference 2009) ለካፈል ለሚመጡት ርዕሰ ብሐሮች ልናስረዳ ተነስተን ወደ ዴንማርክ፣ ኮፐንሀገን (Copenhagen) ሄድን። በዚያ ከሌሎች የአውሮፓ አገሮች ከመጡት ወንድሞችና እህቶች ጋር ሁነን ለሁለት ቀናት ሰላማዊ ሰልፍ አድርገን ስንጓዝ ውለን ስንጓዝ አድረን ወደ ሎንዶን ታኅሳስ 19 ቀን ተመለስን። በነጋታው አስደንጋጭ ዜና ከሆስፒታል ደረሰን። የወንድማችንን ማረፍ ሰማን! ወንድማችን፣ የትጋል አጋራችን፣ የብዙ ሰው አለኝታ፣ አቶ አሰፋ ተስፋዬ በተውለደ በ56 ዓመቱ በፍረንጆቹ አቆጣጠር ታኅሣስ 19 ቀን 2009 ዓ. ም. ከዚህች መከረኛ ዓለም ተሰናበተ።

የለንደን ኗሪ ኢትዮጵያውያን ሕብረተሰብ፣ በተለይ የርዕሰ አድባራት ድብርጽዮን ቅደስት ማርያም ቤትክርስቲያን አባላትን፣ የኢትዮጵያ የጤና ድጋፍ ማህበር፣ የሲቪክ ማኅበራት ስብስብ አባላት እና ወዳጅ ጓደኞቹ በከፍተኛ ኃዘን ተውጠናል። ወንድማችንን አጥተናል። ደግ፣ ትሑት፣ አስተዋይ፣ መካሪ ጓደኛ በሞት ተለይቶናል። በዚህ አጋጣሚ አስከሬኑን ለአገሩ አፈር እንዲበቃ ለለፋችሁና የገንዘብም ሆነ የጉልበት አስተዋጾ ላደረጋችሁ ጓውደኞቹ፣ የበተ ክርስትያን አባላት አንዲሁም ሌሎችም ለወገን የቆማችሁ ኢትዮጵያውያን ላደረጋችሁልን እርዳታ ከልብ እናመሰግናለን።

አቶ አሰፋ ተስፋዬ የአንዲት ሴት ልጅ አባት ነው። ወንድማችንን ምንጊዜም አንረሳውም። ነበስ ይማር።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com